# የአማራና የኦሮሞ የፖለቲካ ፓርቲዎች

## የጋራ የፖለቲካ አቋሞች

መስከረም 13 ቀን 2013

የአማራና የኦሮሞ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ተጋባዥ እንግዶች በሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነትና የጋራ ጉዳዮች ከታህሳስ 2012ዓ.ም. ጀምሮ ተደጋጋሚ ውይይቶችን ስናካሂድ ቆይተናል። በጉባኤዎችና በተጨማሪም የፓርቲዎቹ መሪዎችም በየጊዜው ተገናኝተው ሁለቱን ወገኖች በሚመለከቱ፣ እንዲሁም አገራዊ በሆኑ ነባራዊና ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ስንለዋወጥ ሰንብተናል። የሁለቱ ሕዝቦች ግንኙነት በአሁኑ ወቅት ካለው አገራዊ ሁኔታ አንፃር ከምንግዜውም በላይ የበለጠ ውይይትና ምክክር የሚጠይቅ መሆኑን በመገንዘብ ከበርካታ ጉባኤዎችና የፓርቲ መሪዎች ውይይቶች በኋላ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ የጋራ መግባባት ላይ ደርሰናል።

1. የአገራችንን የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ሁሉን አካታች የሆነ ቀጣይ አገራዊ ውይይትና ድርድር ማካሄድ፣
2. ጥርጣሬ፣ መከፋፈል፣ እርስበርስ መቃረን፣ ወደ ዳር መገፋፋት፣ አንዱ የሌላውን ስም ከማጥፋት እንዲሁም ሕዝብ ለሕዝብ ከሚያጋጩና ከሚያቃቅሩ ድርጊቶች መቆጠብ፣
3. አገራዊ የሕዝብ ቆጠራ ተዓማኒነትና ተቀባይነት ባለው አሠራር በማካሄድ የሁሉም የአገሪቱ ብሔርና ብሔረሰቦች የህዝብ ብዛት በአግባቡ ተቆጥሮ እንዲታወቅ ማድረግ፣ የከዚህ በፊት ግድፈቶች የሚያርምና የማይደገምበት መሆኑን ማረጋገጥ፣
4. በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን መገንባት፣ የግልና የቡድን መብቶችን ማስከበርና በየጊዜውና በየደረጃው ነፃና ፍትሃዊ ምርጫን ማካሄድ፣
5. የኢትዮጵያ የታሪክ አቀራረብ የታሪክ አንጓዎችን ተከትሎ ከሁሉም ብሔርና ብሔረሰቦች በተውጣጡ የታሪክ ምሁራን የአገሪቱን ሕዝቦች ግንኙነትና ታሪክ ጥናት እንዲካሄድ፣ የብሔረሰቦች ጥናት ተቋም (Institute) ማቋቋም፣
6. በኦሮሞና አማራ ክልሎች የሚኖሩ የሁሉም ሕዝቦች አባላት ደህንነትና መብቶች እንዲከበሩ፣
7. በአገራችን በሁሉም አካባቢዎች ሰላምና ፀጥታ፣ ሕግና ፍትሕን ማስፈን፣ ከየቦታው ያለአግባብ የተፈናቀሉ ዜጎች ወደ ቄዬአቸውና ኑሮአቸው እንዲመለሱ እንዲደረግ፣
8. አገሪቱ የምትተዳደርበት ሕገ-መንግስት ሁሉን አሳታፊ በሆነ መንገድ እንዲሻሻል ማድረግ፣
9. በአገሪቱ ዘላቂና ፍትሐዊ የኢኮኖሚ ልማት (Sustainable and equitable economic development) ማጎልበት፣ የሕዝቦቻችንን ፍትሐዊ የኦኮኖሚና የሀብት ተጠቃሚነት ማረጋገጥ፣
10. የተለያዩ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቶችንና ትብብሮችን የሚያጠናክሩ ዝግጅቶችን በጋራ ማዘጋጀት፣

ሁለቱ ወገኖች በበርካታ የእያንዳንዱን ሕዝብ ብሶትና አንገብጋቢ ጥያቄዎች በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት አካሂደናል። ከላይ የተጠቀሱት የፖለቲካ አቋሞች ሁለቱ ወገኖች በጋራ የተስማማንባቸው ሲሆኑ፣ በተቀሩት ጉዳዮችም ላይ ተመሳሳይ ውይይቶችን ለመቀጠልና መላ ሕዝቦችንና አገሪቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ሰፊና ሁሉን አቀፍ አገራዊ ምክክር እንዲደረግ ተስማምተናል። በመጨረሻም ሁለቱም ወገኞች ለዛሬው ታሪካዊ ስምምነት ለመድረስ ነፃና ገለልተኛ የሆኑት አስተባባሪዎች ላበረከቱት አስተዋጽኦ ከፍያለ ምስጋናችንን አቅርበናል።

**የአማራና የኦሮሞ ፖለቲካ ፓርቲዎች፣**

# የጋራ የፖለቲካ አቋሞች ላይ የተሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ስምና ፊርማ

________________________
የአማራ ብሔራዊ ንቅናቄ

________________________
የመላ አማራ ህዝብ ፓርቲ

________________________
ነፀብራቅ አምሐራ ድርጅት

________________________
መላው አማራ ሕዝብ ድርጅት

________________________
የአማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት

________________________
አማራ ዲሞክራሲያዊ ኃይል ንቅናቄ

________________________
የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

________________________
የኦሮሞ ፌደራሊስት ኮንግረስ

________________________
የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ውህደት

________________________
የኦሮሚያ ብሔራዊ ፓርቲ

________________________
የኦሮሚያ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ቅርንጫፍ

________________________
የአማራ ክልል ብልፅግና ፓርቲ ቅንጫፍ